# በፈጣን የለውጥ ግስጋሴ የታጀበው
# የኢትዮጵያ ህዳሴ

`

በሃይሉ ምንተስኖት -ከአዲስ አበባ

ኢትዮጵያ ባለፉት ስምንት አመታት ያስመዘገበችውን ፈጣንና ተከታታይነት ያለው ኢኮኖሚያዊ እድገት ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የአለምዓቀፍ የመገናኛ ብዙሃን ትኩረት ሰጥተው ሲዘግቡት እያዳመጥንና እየተመለከትን ነው ፡፡አይጋ ፎረም ድረ ገፅ በተለያዩ ጊዜያት እነዚህ የአለም ዓቀፍ ሚዲያዎች ኢትዮጵያን አስመልክቶ በየጊዜው በማውጣት ላይ ያሉትን አዎንታዊ ዘገባና ሪፖርት ሳይጨምርና ሳይቀነስ በየጊዜው በድረ ገፁ ላይ ይፋ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ አሁንም በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡በመሆኑም ድረ ገፁ አገር ወዳድ ለሆነው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሁሉ አገሩ ያለችበትን ወቅታዊ ሁኔታ ከማሳወቅ በተጨማሪ የአገሪቷን ገፅታ ለመገንባት በሚደረገው ጥረት እየተጫወተ ላለው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለኝን አድናቆት በዚህ አጋጣሚ ልገልፅ እወዳለሁ፡፡

ቀደም ሲል ወደ ጀመርኩት ርእሰ ጉዳይ ስመለስ የአለምዓቀፍ መገናኛ ብዙሃን ጋዜጠኞች አሁን አሁን ያለማቋረጥ በሚባል ሁኔታ ተከታታይነት ባለው መልኩ እያሰራጯቸው ካሉ ዘገባዎች መረዳት የሚቻለው በአጠቃላይ ኢትዮጵያ እያስመዘገበች ያለችውን ኢኮኖሚያዊ እድገት ጨምሮ በመሠረተ ልማት፣ በግብርና፣ በጤናውና በትምህርቱ ዘርፍ ያሳየችውን እምርታና ከፍተኛ ለውጥ ከማንም ሊደበቅና መካድ ያልተቻለ ገሃድ እየሆነ መምጣቱን ነው፡፡

በአገሪቱ የመንገድና የኤሌክትሪክ ሃይል ግንባታን ጨምሮ የተለያዩ መሠረተ ልማቶች እንዲስፋፉ ባለፉት አመታት የተመዘገበው ባለሁለት አሀዝ የኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡በመሆኑም በአሁኑ ወቅት አዲስ አበባን ጨምሮ በክልሎች ዋና ዋና ከተሞች እየተካሄደ ያለው ከፍተኛ የኮንስትራክሽን ግንባታ ከተሞቹ በእጅጉ እንዲለወጡና እንዲሻሻሉ አድርጓል፡፡ይህም የተለያየ መገናኛ ብዙሃንን ትኩረት ሊስብ በቅቷል፡፡

በመሆኑም የአሁኗ ኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ግንባታ እንደ አሸን የፈለባት፣ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ፣ የባቡር መንገድ ዝርጋታና የተለያዩ መሰረተ ልማት ግንባታዎች የተጧጧፉባት፣ ለዜጎች የአገልግሎት መስጫ የሆኑ የጤናና የትምህርት ተቋማት እየተስፋፉ ያሉባት፣ አገር ሆና በመገናኛ ብዙሃን እንድትቀርብ በአገሪቱ የሚታየው ተጨባጭ ሁኔታ ማስገደዱን ከተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ዘገባዎች እየተረዳን ነው፡፡

አለምዓቀፍ የመገናኛ ብዙሃን በቀድሞ ዘገባቸው ኢትዮጵያን የድህነትና የርሃብ ተምሳሌት አድርገው ለማሳየት ይጠቀሙበት የነበረውን የቋንቋና የአገላለፅ ዘይቤ ለማስወገድ ዳር ዳር እያሉ መሆናቸውን በእርግጠኝነት መናገር የሚቻልበት ወቅት ላይ እየደረስን ነው ለማለት ያስገደዱኝን አንዳንድ አገላለፆች በዚህ ፅሁፍ ለአብነት እጠቃቅሳለሁ ፡፡

**በቅርቡ በጃንዋሪ 25/2012 በዘ ኢኮኖሚስት ብሎግ** “Ethiopia ; Galloping Ahead” By J. L. **በሚል ባሰፈረው ፅሁፍ** *“አፍሪካ በአሁኑ ወቅት በእድገት ምህዋር ውስጥ ትገኛለች።የአህጉሪቱ ይህ ፈጣን እድገትም በገሃድ እየታዬ ያለው በኢትዮጵያ ሲሆን በተለይም የኢትዮጵያ መዲና አዲስ አበባ በከፍተኛ ሁኔታ እየተመነደገች ነው”* ይላል ዘጋቢው ።

**ዘ ኢኮኖሚስት በዚህ ፅሁፉ ላይ አያይዞም** *ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ወደ ኢንዱስትሪ እድገት ለመሸጋገር በመጀመሪያ ደረጃ ላይ ትገኛለች ሲል ገልፆ ኢትዮጵያን ለመመልከት እንጦጦ አካባቢ ያሉ ትናንሽ የገጠር አካባቢዎችን ማየቱ በቂ ነው። በእነዚህ አካባቢ ዙሪያ ርሃብም ሆነ የምግብ እጥረትም አይታይም ሲል አስፍሯል።*ኢትዮጵያ ውስጥ ባደረገው ቆይታ የተመለከተውንና የታዘበውን ሲገልፅ።

በአሁኑ ወቅት የተለያዩ የውጪ አገራት መገናኛ ብዙሃን ወኪሎችም ሆነ ጋዜጠኞች አዲስ አበባ ውስጥ በየጊዜው የሚካሄዱ አለምዓቀፍና አህጉራዊ ስብሰባዎችን ለመዘገብ በተለያዩ ጊዜያት ወደ አገሪቱ መመላለሳቸው አልቀረም። ከዚህ ጋር ተያይዞ እነዚህ ጋዜጠኞች በየጊዜው ወደአገሪቱ ጎራ ባሉበት ወቅት በተለይም

በመሠረተ ልማቱና በኮንስትራክሽን ግንባታ ዘርፍ በየጊዜው የሚመለከቱት ለውጥና መሻሻል  የፈጠረባቸው ግርምት ስለ አገሪቱ ለመፃፍ እንዳስገደዳቸው በመጥቀስ ያሰራጯቸውን የተለያዩ ዘገባዎች እያነበብን እየተመለከትንና እያደመጥን ነው፡፡

ለዚህ እንደ አብነት የምጠቅሰው እዚሁ አይጋ ፎረም ድረ ገፅ ላይ ሰፍሮ ያነበበኩት በኡጋንዳው ዴይሊ ሞኒተር ጋዜጠኛ Joachim Buwembo የኢትዮጵያ እድገትን አስመልክቶ የቀረበን አርቲክል ነው፡፡ጋዜጠኛ Joachim Buwembo ኢትዮጵያ ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ በመሰረተ ልማት ግንባታውና በኮንስትራክሽን ማስፋፋት ዘርፍ የሚታየው እምርታና ለውጥ ሚስጥሩ ምንድነው ሲል ይጠይቃል፡፡ ጋዜጠኛው ኢትዮጵያ የነዳጅ ምርት የሌላት አገር እንደሆነች እየታወቀ የታላቁን የህዳሴ ግድብ ግንባታ ጨምሮ በየጊዜው የምታካሂዷቸው ግዙፍ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግንባታዎችና እንዲሁም የተለያዩ መሰረተ ልማት መስፋፋቶች ግርምትን እንደፈጠረበት ያሰፈረው ከጥቂት ወራት በፊት ነበር፡፡

የኡጋንዳው ጋዜጠኛ የኢትዮጵያ እድገት ለአገሩ ኡጋንዳም ትምህርት እንዲሆን ከመመኘት በመነጨ ቀና ስሜት ኢትዮጵያ ውስጥ የተዋወቀውን ጓደኛውን “እናንተ ኢትዮጵያውያን እኛ ኡጋንዳውያን በነዳጅ ያላገኘነውን እድገት እናንተ እንዴት ያለ ነዳጅ ልታስመዘግቡት ቻላችሁ?” ሲልም በአድናቆት ጠይቆት እንደነበር በፅሁፉ ጠቅሷል፡፡

በኢትዮጵያ የሚካሄዱ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን በአካል ተገኝተው ለመዘገብ ለሚፈልጉ የተለያዩ የውጪ አገራት መገናኛ ብዙሃን ወኪሎችና ጋዜጠኞች በአገሪቱ ከመቼውም ጊዜ በላይ ይህንን ተግባራቸውን ለማከናወን የሚያስችላቸው ምቹ ሁኔታ እንደተፈጠረላቸው የሚታወቅ ነው ፡፡በመሆኑም በአገሪቱ ባስፈለጋቸው ጊዜ ገብተው አሊያም የመገናኛ ብዙሃን ተቋማቸው ቋሚ ተወካይ ሆነው ዘገባዎችን ቀደም ሲል በተጠቀሰው መልኩ እያስተላለፉ አለምዓቀፉ ማህበረሰብ ኢትዮጵያን አስመልክቶ ተገቢው መረጃ እንዲኖረው በማድረግ በኩል የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞም በቅርቡ የቢቢሲ ቴሌቪዥን በአዲስ አበባ የገበያ ስፍራዎችና የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች በሚካሄዱባቸው የባንክና መሰል ተቀሟት ላይ ተገኝቶ በምስል በማስደገፍ ያሰራጨው ዜና እንዲህ ይል ነበር ። “ኢትዮጵያ በፈጣንና በተከታታይ ሁኔታ እያስመዘገበች ያለውና በመጪዎቹ አመታትም ታስመዘግባለች ተብሎ በአለምዓቀፍ የገንዘብ ተቋማት የተተነበየው እድገት ቻይና በመጀመሪያዎቹ አስርት አመታት ማስመዝገብ ከጀመረችባቸው ወቅት ከታየው እድገት ጋር የሚመነፃፀር ነው” ነበር ያለው።

ኢትዮጵያ በዓለማችን በፍጥነት በማደግ ላይ ከሚገኙት አገራት ተርታ የምትገኝና በሚያስደንቅ ሁኔታ በለውጥ ጎዳና ላይ ያለች መሆኗም በአሁኑ ወቅት ገንዘባቸውን በአፍሪካ ማፍሰስ የሚፈልጉ የውጭ ባለ ሀብቶችን ትኩረት መሳብ እንድትችል እንዳደረጋትም ነበር አያይዞ የገለፀው ፡፡

የእነዚህ መገናኛ ብዙሃን ዘጋቢዎች የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ እድገት ለማሳየት በአለም ላይ ፈጣንና ተከታታይ የሆነ ኢኮኖሚያዊ እድገት በማስመዝገብ ከድህነት ከወጡ ቻይናን ከመሰሉ አገራት ጋር ካደረጉት ንፅፅር በተጨማሪ በአገሪቱ የግብርናው፣ የማህበራዊ አገልግሎት ማለትም የጤናና የትምህርቱን እንዲሁም የመሰረተ ልማቱንና የተለያዩ ዘርፎች ላይ የተመዘገበው ስኬት ላይ አተኩረው የዘገቡበት ሁኔታም ይስተዋላል።

በቅርቡ ማርክ ትሬይን የተባለው የዘጋርድያን ጋዜጣ ዘጋቢ በርካታ የአፍሪካ አገራት ስምምነት ላይ የደረሱት ከአጠቃላይ አገራዊ ኢኮኖሚያቸው ውስጥ 10 በመቶ ያህሉን ለግብርናው ዘርፍ ለማዋል ቢሆንም ኢትዮጵያ ግን ከሌሎች አገራት በተለየ ሁኔታ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ለማምጣት በያዘችው እቅድ በአምስት አመቱ የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅዷ ከአጠቃላይ በጀቷ በየአመቱ 17 በመቶ ያህሉን ለዚህ ዘርፍ መድባለች ይላል ፡፡

ዘጋቢው አያይዞም ከአዲስ አበባ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ 352 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው የድሬዳዋ ከተማ ዙሪያ ያሉ የገጠር አካባቢዎች በግብርና ሙያ

ላይ የተሰማሩ አርሶ አደሮች የእለት ተእለት የስራ እንቅስቃሴ በአካል ተገኝቶ መመልከቱን ይገልፃል፡፡ ዘጋቢው በእርሻ ማሳቸው በስራ ላይ እያሉ የተመለከታቸው የ72 እድሜ አዛውንት ዳዲ ያደቴ የተባሉ አርሶ አደር ትኩረቱን ስለሳቡት እንዳነጋገራቸው በድረ ገፅ ላይ አስፍሯል፡፡

በድሬዳዋ ከተማ ዙሪያ ያሉ የገጠር አካባቢዎች ለበርካታ አመታት የማሽላ ምርት የብዙዎቹ የአርሶ አደሮች መተዳደሪያ የግብርና ምርት ሆኖ መቆየቱን እንደገለፁለት ያሰፈረው ዘጋቢው ከቅርብ አመታት ወዲህ ግን በዚሁ አካባቢ የማሽላ ምርት በአፕል ምርት መቀየሩን ተመልክቻለሁ ብሏል፡፡

አዛውንቱ አርሶ አደርም ባነጋገራቸው ወቅት ከሶስት አመት በፊት ከዚህ በፊት ተክለው የማያውቁትን የአፕል ዘር ከአካባቢው ግብርና ቢሮ ወስደው መትከል መጀመራቸውን እንደገለፁለት አመልክቷል፡፡አዛውንቱም የአፕል ምርቱን ለመትከል ወደ ማሳቸው በወሰዱበት የመጀመሪያው ወቅት በማመንታትና በጥርጣሬ ተሞልተው 12 ግንድ አፕል መትከላቸውንና ውጤቱ ግን ከጠበቁት በላይ እጅግ አስደሳች እንደነበር እንደገለፁለት ያብራራል፡፡

በኢትዮጵያ ከፍታማ ቦታ ከባህር ወለል በላይ 2 ሺህ 300 ሜትር ላይ የሚገኘው የድሬዳዋ አካባቢ እጅግ ቀዝቃዛማም ሞቃታምም ሳይሆን መካከለኛ የሆነ የአየር ንብረት ያለው መሆኑ ለአፕል ምርቱ ተስማሚ እንዳደረገው ዘጋቢው ምልከታውን ይገልፃል፡፡

በዚህም እንደ አርሶ አደር ዳዲ ያደቴ ሁሉ በርካታ የአካባቢው አርሶ አደሮችም አፕል በማምረት ተጠቃሚ መሆናቸውን ይገልፃል፡፡የዘጠኝ ልጆች አባት የሆኑት አርሶ አደር ዳዲ ያደቴ ባለቻቸው 0 ነጥብ 5 ሄክታር በሆነች አነስተኛ መሬታቸው 70 የአፕል ግንድና በርካታ የአቮካዶ ምርት ግንዶችም ፍሬ አፍርተው ይታያሉ ብሏል፡፡ አርሶ አደር ዳዲ ያደቴ ማሳ ላይ ከአፕል ምርት በተጨማሪ የቡና ምርት፣ የስኳር ድንች፣ ቃሪያና የሚጢሚጣ ዘለላዎችንም መመልከቱን በግርምት ይገልፃል፡፡

አዛውንቱ አርሶ አደር ማሽላና ገብስ ያመርቱ በነበረበት ወቅት ህይወት አስቸጋሪ እንደነበረባቸውና በዚያ ወቅትም ምርት አመርታለሁ ማለት አይቻልም ነበር እንዳሉት የሚገልፀው ጋዜጠኛው ማሽላና ገብስ አመርት በነበረበት ወቅት የምግብ እርዳታ እቀበል ነበር፡፡ ሆኖም አሁን ግን በአተል ምርት ብቻ እስከ 600 ዶላር በወራት ውስጥ ስለማገኝ እርዳታ መቀበሌ ታሪክ ሆኗል እንዳሉት በፅሁፉ አመልክቷል፡፡

ኢትዮጵያ በሚቀጥሉት አምስት አመታት ግብርናውን በ8 ነጥብ 1 በመቶ ለማሳደግ በያዘችው እቅድ የሰብል ምርቷን አሁን ካለበት የ18 ነጥብ 1 ሚሊዮን ቶን ወደ 39 ነጥብ 5 ሚሊዮን ቶን ለማሳደግ እቅድ ይዛ እየተንቀሳቀሰች ነው ሲልም ጋዜጠኛው አያይዞ አስፍሯል፡፡

በኢትዮጵያ ባለፉት ስምንት ተከታታይ አመታት የተመዘገበው ባለሁለት አሀዝ አጠቃላይ አገራዊ የኢኮኖሚ እድገትም 45 በመቶው ከግብርናው ዘርፍ የተገኘ መሆኑን የጠቀሰው ማርክ ትሬይን ይህ ዘርፍ ለ80 በመቶው ያህል የአገሪቱ ህዝብ ደግሞ የስራ እድል የፈጠረ ነው ሲልም በዚሁ ዘገባው አመልክቷል፡፡

ማርክ ትሬይን በተለይም ከግብርናው ትራንስፎርሜሽን ጋር አያይዞ የአንድ አርሶ አደርን የእለት ውሎ በመዘገብ ሊያሳየን የሞከረው እንደ እኔ አተያይ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ገብስና ማሽላን የመሰሉ የሰብል ምርቶችን ብቻ በማምረት ተወስነው የነበሩበት ሁኔታ ተቀይሮ በአነስተኛ ማሳ አራትና አምስት አይነት በገበያ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን ማምረት መጀመራቸቸው ከእርዳታ ጠባቂነት እንዲወጡ እንዳደረጋቸውና ገቢያቸ እንዲጨምር እንዳደረገላቸው ነው ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም አርሶ አደሩ በገበያ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን ማምረት መጀመሩም አገሪቱ ለውጭ ገበያ የምትልከው የምርት መጠን በዓመት 50 በመቶ እንዲጨምር እንዳደረገው  ቀደም ሲል የጠቀስኩት የዘ ኢኮኖሚስት ጋዜጠኛ ሲገልፅ ሆኖም የብር ዋጋ እንዲቀንስ (Devaluate) መደረጉም ለዚህ እድገት ተጨማሪ አስተዋፅኦ አበርክቷል ይላል።

በኢትዮጵያ ከሚኖረው 85 ሚሊዮን ያህል ህዝብ 80 በመቶ ያህሉ አርሶ አደር ከመሆኑ አንፃር የአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል የተሰማራበት ይህ ዘርፍ መንግስት በቀየሰው ፖሊሲ በገበያ መር ስትራቴጂ እንዲመራ መደረጉ በአርሶ አደሩ የአኗኗር ዘይቤ ላይ ከፍተኛ የሆነ ለውጥ አምጥቷል።

ቀደም ሲል እንደተገለፀው በኢትዮጵያ አርሶ አደሩ በገበያ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን እንዲያመርት በስፋት የተደረገ ሲሆን ምርቱን ካመረተ በሁዋላ ግን "በፈለገህ መንገድ ሽጠው አሊያም ተወጣው" በሚል የገበያ ማፈላለጉ ጉዳይ በአርሶ አደሩ ትከሻ ላይ ብቻ የተጫነ አይደለም። ይልቁንም አርሶ አደሩ ባመረተው ምርት መጠን የልፋቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መንግስት ለአርሶ አደሩ ምርት ገበያ ማፈላለጊያ የሚሆን ማእከል መስርቶለታል። የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት የተሰኘ ተቋም ለዚሁ አላማ ከተመሰረቱት ተቋማት አንዱ ነው።

የዘጋርድያን ዘጋቢ አሌክስ ፔሪ በዚሁ ተቋም አርሶ አደሩ የሚያካሂደውን የምርት ግብይት ከተመለከተ በሁዋላ " Africa Bloosom" በሚል ባወጣው ዘገባ በዛሬዋ ኢትዮጵያ በሁሉም ዘርፍ የሚታየውን ለውጥ ለተመለከተ በከፍተኛ አድናቆት ይመሰጣል ሲል ነበር ያሰፈረው ።ከሃያ አምስት አመት በፊት በርሃብ የተጎዱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎቿን ለመታደግ የላይቭ ኤይድ እርዳታ ተቀባይ የነበረችው አገር በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የምርት ገበያ አማካይነት ለአለም ገበያ ካቀረበችው የቡና ሰሊጥ አኩሪ አተርና በሎቄ ምርት ሽያጭ በአንድ አመት የአንድ ቢሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘቷ እጅግ የሚገርም ነው ይላል።

ይህ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት በኩል መካሄድ የጀመረው ዘመናዊ የግብርና ምርት ገበያ ስርዓት በአገሪቱ በግብርናው ዘርፍ ከሰብል ምርት ወደ ገበያ ተፈላጊ የሆኑ ምርት ማምረት የተደረገ ከፍተኛ ሽግግር ነውም ብሎታል ዘጋቢው በፅሁፉ።ይህም ዘመናዊ የግብይት ስርአት ለሌሎች የአፍሪካ አገራት የግብርና ዘይቤ ከፍተኛ አርአያነት እንዳለው አመልክቷል። አርሶ አደሩ ለገበያ ፍጆታ የሚውሉ ምርት እንዲያመርት መደረጉ የሚያስገኘው ጥቅም የሰብል ምርት ያመርት

ከነበረበት ጊዜ ይልቅ ምርታማነቱን ለማሳደግ የስራ ተነሳሽነቱ እንዲጨምርና መሬቱንና የምርት ግብአቱንም በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲያውል እንደሚያደርገውም ይገልፃል።ይህም አርሶ አደሩን ከመቼውም ጊዜ በላይ በአገራዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ያደርገዋል።

እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ በአፍሪካም አርሶ አደሩ በሰብል ምርት ብቻ መወሰኑን አቁሞ ይበልጥ በገበያ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን ጭምር ወደ ማምረት እንዲሸጋገር ማድረግ ቢቻል በአፍሪካ በከፋ ድህነት ውስጥ የሚኖሩ ዜጎችን ቁጥር እንደሚቀንስ የአለም የምግብ ሪሰርች ተቋምና የአለም ባንክ ባካሄዱት ጥናት መጠቆማቸውን በመጥቀስ ዘጋቢው በፅሁፉ አስፍሯል።የተቋማቱ ጥናት የአርሶ አደሩ የግብርና ምርት ገቢ በፊት ከነበረው በአንድ በመቶ ብቻ መጨመር ከተቻለ እንኳን በከፋ ድህነት የሚኖሩ ዜጎችን ቁጥር ከ0 ነጥብ 6 እስከ 1 ነጥብ 8 በመቶ እንደሚቀንስ በጥናታቸው ማረጋገጣቸውንም ጨምሮ ገልጿል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ከጥቂት ወራት በፊት አዲስ አበባ ውስጥ የአፍሪካ መንግሥታት ሚኒስትሮችና የተለያዩ አገራት የግብርና ባለሙያዎች በተሳተፉበት የግብርና ጉባኤ ላይ በአፍሪካ የግብርና ዕድገት የመረጃ ሥርጭት ለውጥ እያመጣ መሆኑን መገለፁንም የተለያዩ ሚዲያዎች ዘግበዋል። ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያ ገበሬዎች ስልክ ደውለው የምርት ዋጋ የሚጠይቁበት የስልክ የመረጃ አገልግሎት መጀመሩ ለሌሎች የአፍሪካ አገራትም ምሳሌ ሆኖ በዚሁ ወቅት መጠቀሱንም ጠቁመዋል፡፡

በተለይም ይህንን አገልግሎት የሚሰጠው የኢትዮጵያ የምርት ገበያ ከተመሠረተ ከሦስት ዓመታት ወዲህ ገበሬዎች በገበያ የመደራደር ችሎታቸውን ለመገንባት ማስቻሉ ተረጋግጧል ያሉት ሚዲያዎቹ በዚህ ዉይይት ላይ በኢትዮጵያ የታየው የምርት ገበያ መደራጀት እመርታ በእነርሱም አገር ይሰራ እንደሆነ ለመሞከር በርካታዎቹ ተሳታፊዎች ጓጉተዋል ሲሉም ነበር ያመለከቱት፡፡

የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም (UNDP) ይህ ዓለም አቀፍ ትኩረትን የሳበው የኢትዮጵያ የግብርና ምርት ገበያ ስርአት ተሞክሮ ተሞክሮ ከኢትዮጵያ

ምርት ገበያ ጋር በመተባበር በሌሎች የአፍሪካ አገሮች ተግባራዊ ለማድረግ የልምድ ልውውጥ እንዲካሄድ በመጣር ላይ መሆኑንም አመልክተዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያን የመንብኘት አጋጣሚ ያገኘ የውጭ ዜጋና ጋዜጠኛ ላይ ከፍተኛ አግራሞትን እየፈጠረ ያለው ይህ የአገሪቱ ፈጣን የለውጥና የእድገት ግስጋሴ የአዲስ አበባ አንዳንድ ነዋሪዎች በስራ አጋጣሚ አሊያም በሌላ ምክንያት ለጥቂት ቀናት ብቻ እንኳን ከአገር ወጥተው ሲመለሱ “’ሰፈሬን አፉልጉኝ” እያሰኘ ነው ሲሉ እንዲቀልዱ አድረጓቸዋል የአዲስ አበባ ነዋሪዎችን፡፡

በገጠር ያለውን ስንመለከት ደግሞ ከአንድ ባልደረባዬ ጋር ለመስክ ስራ በቅርቡ በኦሮሚያ ክልል ባሉ የገጠሩ ክፍሎች በተገኘንበት ወቅት በቅርብ አመታት ውስጥ ልጆች ሆነን የአርሶ አደር ቤት በሚል የምናውቀውን የሳር ጎጆ  አይናችን ቢፈልግ ቢፈልግ ሊያገኘው አልቻለም፡፡በዚህን ጊዜ አጠገባችን ሆኖ ጨዋታችንን በጥሞና ያደምጥ የነበረው የመኪናችን አሽከርካሪ የሳር ጎጆ እኮ በአሁኑ ወቅት በኦሮሚያ ክልል ብቻ ሳይሆን በአገሪቱ ባሉ የተለያዩ የገጠሩ ክፍሎችም ብትዘዋወሩም ልታገኙ አትችሉም በሚል እሱ በስራ አጋጣሚው የታዘበውን መልሶ አወጋልን ፡፡ በአሁኗ ኢትዮጵያ በርካታ አርሶ አደሮች ያማሩና የተዋቡ የብሎኬት ቤቶችን ገንብተው መኖራቸው ብቻ ሳይሆን ከእርሻ ማሳቸው በተጨማሪ የከባድ መኪናዎች ባለቤት ሆነው በተጨማሪም ሆቴሎችንና ሌሎች የንግድ ተቋማትን ገንብተው ማየቱ እንግዳ አሊያም አዲስ ነገር አይደለም፡፡

በአሁኑ ወቅት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሚሊዮነር አርሶ አደሮች እንደሚገኙ ለማረጋገጥ የሚጠይቀው ወደዚያው መንቀሳቀስን ብቻ ነው፡፡ይህም የአሁኗ ኢትዮጵያ ዜጎች ሠርተው በለፉበትና በደከሙበት መጠን የሚያድጉባት ሃብት የሚያፈሩባት በመለወጥና በተስፋ ላይ ያለች አገር መሆኗን ያመላክታል።

ኢትዮጵያን ጨምሮ በአፍሪካ አገራት በአሁኑ ወቅት የሚታየው ኢኮኖሚያዊ እድገት መምጣት ምክንያት የሆኑት ደግሞ በስልጣን ላይ ያሉት የአዲሱ ትውልድ መሪዎች ፣ ቢዝነስ ለመሥራት አመቺ የሆኑ ፖሊሲዎችና የቴክኖሎጂ መኖር፣

የሰላምና መረጋጋት መስፈን ዋና ዋና ምክንያት መሆናቸውን ነበር The Guardian በድረ ገፁ በቅርቡ ባወጣው ዘገባ ያመለከተው፡፡

ሆኖም ኢትዮጵያ ይህን መሰል ፈርጀ ብዙ እድገት በማስመዘገብ ከድህነት ለመውጣት እያደረገች ያለችው ውጤት አበረታች ውጤት እያስመዘገበ ባለበት ወቅት ረገብ እያለ የመጣው የዋጋ ግሽበትንና የኑሮ ውድነትን አይነት ፈተናዎች ቀደም ባሉት ወራት አላጋጠሙም ማለት አይደለም። ይህ ሁኔታ የፈጠረላቸውን ሁኔታም እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀምም የውጭው ማህበረሰብ እንኳን በከፍተኛ ሁኔታ እያደነቀ ያለውን  የአገሪቱ ዘርፈ ብዙ እድገት አንድ ቀን አምነውና ተቀብለው የማያውቁት መድረክና መሰል ተቃዋሚ ነን ባዮች እነዚህን ችግሮች በማራገብ ህብረተሰቡን በብሶት ለማነሳሳት ያልሞከሩበት አንድም ቀን እንዳልነበረ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። ህዝቡ ጆሮውንና ቀልቡን አልሰጣቸውም እንጂ ።

ይልቁንም በአለም ዓቀፍ ከተከሰተው የኢኮኖሚ ቀውስ ጋር ተያይዞ በአገራችንም መጠነኛ በሆነ መልኩ ቀደም ባሉት ወራት የተከሰተውን መሰል የዋጋ ግሽበትንና የኑሮ ውድነት ህብረተሰቡ  ቀደም ሲል የተጠቀሰውን ለውጥና እድገት በአገሪቱ ማምጣት የቻለ መንግስት ይህን ችግር መፍታትም አይሳነውም በሚል መፍትሄ ከመንግስት በትእግስት ሲጠብቁ ተስተውሏል ።

በመሆኑም መንግስት እነዚህን ችግሮች ለመቆጣጠር እያደረገ ያለው ጥረት በብዛቱ በኢትዮጵያ ታሪክ ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ከተሰበሰበው ከፍተኛ የሆነ የእህል ምርት መጠን ጋር ተዳምሮ በአሁኑ ወቅት በአንፃራዊነት የዋጋ ግሽበቱ የወረደበት ሁኔታ እየታየ ነው።

ስለሆነም በኢትዮጵያ ላለፉት ስምንት አመታት በፈጣንና በተከታታይ ሁኔታ የተመዘገበው ኢኮኖሚያዊ እድገት ለመጪዎቹ ተከታታይ አመታትም መመዝገቡን እንደሚቀጥል የአለም ባንክም ሆነ ሌሎች የገንዘብ ተቋማት መግለፃቸውን እንደቀጠሉ ናቸው፡፡ከዚህ ጋር ተያይዞም ቀደም ሲል በአገሪቱ በርካታ የሥራ

እድልን በመፍጠር፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የንፁሕ ውኃ፣ የመፀዳጃ አገልግሎቶችን እንደዚሁም የመንገድ አውታሮችን በመዘርጋት ረገድ የተጀመሩና የመጡ ለውጦችም ተጠናክረው የሚቀጥሉ ይሆናሉ ።

ከተፈጠሩ ጀምሮ ሲጮሁና ሲያላዝኑ የምናውቃቸው መድረክና መሰል ነውጠኛ ተቃዋሚዎች ለዚህች አገር እድገት አንዳች አይፈይዱ እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ግን በመላው አለም እየፈነጠቀ ያለው የእድገት ፀሃይ ጮራ ይበልጥ እንዲያበራ አሁንም እጅ ለእጅ ተያይዘው መስራታቸውን ቀጥለዋል። ባልሳሳት ፈረንጆቹ "ውሾቹ ይጮሃሉ ግመሎቹ ግን ጉዟቸውን ቀጥለዋል" የሚሉትስ ይህን አይነቱን አይደል!

ቸር ይግጠመን!